የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሀያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፭ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.21
ADDIS ABABA 3rd May, 2023

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፴፬/፳፻፲፭

በከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን ተግባርና ኃላፊነት እና ጥቅማጥቅምን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........................................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፵፩

## Content

Regulation No. 534/2023

The Roles , Responsibilities and other benefits of Academic Technical Assistants working in Public Governmental Higher Education Institution and Teaching Hospitals Council of Ministers Regulation……………………………… Page 14741

**ደንብ ቁጥር ፭፻፴፬/፳፻፲፭**

**በከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን ተግባርና ኃላፊነት እና ጥቅማ ጥቅምን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፳፻፲፩ አንቀጽ ፴፭/፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ በከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን ተግባርና ኃላፊነት እና ጥቅማ ጥቅምን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፴፬/፳፻፲፭ ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**REGULATION NO. 534/2023**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ROLES, RESPONSIBILITIES AND BENEFITS OF ACADEMIC TECHNICAL ASSISTANTS WORKING WITHIN GOVERNMENTAL HIGHER EDUCATION INSTITUTION AND TEACHING HOSPITALS**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 35 (1) of the Higher Education Proclamation No 1152/2019.

## Part One

## General

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as “The Roles , Responsibilities and other benefits of Academic Technical Assistants working in Public Governmental Higher Education Institution and Teaching Hospitals Council of Ministers Regulation No.534/2023”.

## ፪.<u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውሰጥ፡-

፩/ "**ሚኒስቴር**" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤

፪/"**የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ** " ማለት የመማር ማስተማርን ፣የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ሥራን በሙያው ለማገዝ የተቀጠረ ሠራተኛ ነው፤

፫/ "**የተግባር ትምህርት** " ማለት በቤተ-ሙከራ ፣በወርክ ሾፕ፣ በኢንደስትሪ ውስጥ፣ በልህቀት ማዕከላት፣ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች እና በሌሎች በመስክ በተግባር ተደግፎ የሚሰጥ ትምህርት ማለት ነው፤

፬/"**ቤተ-ሙከራ**" ማለት ለተፈጥሮ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ ፣የቴክኖሎጂ ትምህርት እና ሌሎች የተግባር ትምህርት ላላቸው የትምህርት ክፍሎች በአንድ ክፍል በተደራጁ መሳሪያዎች በመጠቀም ሙከራ የሚደረግበት ክፍል ነው፤

፭/ "**የማስተማሪያ ሆስፒታል** " ማለት ባለቤትነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ የሆነ የጤና አገልግሎትን ከመማር ማስተማርና ምርምር ጋር አጣምሮ የሚሰጥ ሆስፒታል ማለት ነው፤

፮/ "**የመስክ የተግባር ትምህርት**" ማለት ለተፈጥሮ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትምህርትን በተግባር አስደግፎ በመስክ የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

፯/ "**ወርክሾፕ** " ማለት የተለያዩ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን የያዘ የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን በመጠቀም ተግባራዊ ትምህርት የሚሰጥበት ክፍል ነው፤

## 2. <u>Definition</u>

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ **"Ministry"** means the Ministry of Education;

2/ "**Academic Technical Assistance"** means personnel employed to support the teaching-learning, research and Community Service by his profession;

3/ **"Practical Teaching"** Means teaching-learning process supported by practice and teaching in workshop, laboratories, industrial linkages, excelling centers, teaching hospitals and others field works;

4/ **"Laboratory"** means a room whereby scientific research is practically provided in organized equipment's for the field of natural science, social science and technological education;

5/ **"Teaching Hospital"** means a hospital owned and operated by Higher Education Institution that accomplishes a joint Teaching, Service and Research Activities.

6/ **"Field Education"** shall mean a system whereby scientific education and research is carried out by physically presenting on field for research and social activities of natural science, social science and technological education;

7/ "**Workshop"** means a room whereby practical education, research and studies as well as social service is provided through availing ourselves of science and technological equipment's holding various tools and machineries;

፰/"**የሙያ ሥልጠና ትምህርት** " ማለት ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን የንድፈ ሐሳባዊ ትምህርት በላቦራቶሪዎች ፣ በዎርክሾፖች እና በመስክ ወይም በኢንዱስትሪዎች በተግባራዊ ሥልጠና ፣ የተግባር ሥልጠና እና ግምገማ ማለት ነው ፤

፱/ የፆታ አገላለፅ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ የሴት ፆታንም ያጠቃልላል፡፡

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. ዓላማ**

በከፍተኛ ትምህርት በመንግሥት ተቋማት ውስጥ በላቦራቶሪዎች ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በልህቀት ማዕከላት ፣ በመስክ ልምምድ፣ በምርምር ማዕከላት እና በማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች አገልግሎትን ለመስጠት፣ ለማሻሻል እና ውጤታማነትን ለማሳደግ በዋነኛነት የባለሙያዎችን ጥቅምና መብቶች በማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ተልዕኮ በውጤታማነት እዲሳካ ለማድረግ ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ መብትና ግዴታዎች**

**፭. አካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ መብት**

የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በተሰማራበት ሥራ ሙያውን ለማሳደግ የረጅም ጊዜ እና አጫጭር ሥልጠና የማግኘት፤

፪/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ ጥቅማ ጥቅም፣ የደረጃ ዕድገትና ማበረታቻ፣ የማግኘት፤

፫/ የሚሰማራበትን የሥራ ቦታ ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ተጋላጭነት አበል የማግኘት፤

8/ **"Apprenticeship Education"** means providing practical training, apprenticeship and evaluation of student of the theoretical thoughts given to them by attending into laboratories, workshops and fields or industries;

9/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of Application**

This Regulation shall apply on Academic Technical Assistants working within Public Governmental Higher Education Institutions and Teaching Hospitals.

**4. Objective**

Provide services, improve and increase efficiency in laboratories, industry, centers of excellence, field practice, research centers and community service areas in higher education institutions, primarily by ensuring the benefits and rights of professionals to achieve the mission of higher education effectively.

**Part Two**

**Rights and Obligations of Academic Technical Assistants**

**5. Rights of Academic Technical Assistant**

Academic Technical Assistant has the following rights:

1/ Getting long term and short term training to improve his skills in the work he is engaged in;

2/ According to the Directive issued by the Ministry, receiving administrative benefits, promotions and incentives;

3/ Getting an accident allowance that takes into account the place of work;

፬/ በተመሳሳይ ተቋማት ወይም በተመሳሳይ የሙያ መስክና የሥራ መደብ በተቋማቱ ስምምነት ወደ አቻ መደቦችና ሌሎች ተቋማት የመዛወር፤

፭/ የምርምርና የማስተማር ሥራ በተግባር በሚደገፍበትና በሚሰራበት ጊዜ የአካዳሚክ ነጻነት የማግኘት፤

፮/ ከሥራ ሠዓት ውጭ ተጨማሪ ሠዓት ከሥራ የትርፍ ሠዓት ክፍያ የማግኘት፤

፯/ከትምህርት ክፍሎች፣ ኮሌጆች፣ ፋካሊቲዎች ፣ማስተማሪያ ሆስፒታሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመሆን የማቀድና በተቋሙ ተልዕኮ አፈፃጸም ግምገማ ላይ ተሳትፎ ማድረግ፡፡

## ፮. አካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ ግዴታ

የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የተግባር ትምህርት የሚሰጥባቸው የትምህርት ይዘቶችን በመለየት ግብዓቶችና አደረጃጀቶችን በማመቻቸት ትምህርቱ በአግባቡ እንዲሰጥ የማድረግ፤

፪/ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚገኙ ወርክሾፖች፣ ቤተ ሙከራዎች፣ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች፣ በልህቀት ማዕከላት፣ ተማሪዎች የተግባር ትምህርት በሚማሩባቸው ኢንዱስትሪዎች ጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት በሚሰጡባቸው መስኮች የሚጠበቁባቸውን ተግባራት የመፈጸም፤

፫/ ለተግባር ትምህርት የሚያገለግሉ የተለያዩ አይነት ማንዋሎችን በጥራት አዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤ የተዘጋጁ ማኑዋሎችን የመገምገም ብሎም ማስተካከያ የመስጠት፤

፬/ የቴክኖሎጅ እድገትና መሻሻልን በመከተል የላብራቶሪ፣ የመስክ ትምህርትን የላቀ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የማድረግ፤

፭/ የተለያዩ የላብራቶሪና የመስክ የወርክሾፕ መሳሪያዎችን የመረከብ፣ የመጠገንና እዲጠገኑ የማድረግ፣ ከብልሽትና ከብክነት የመጠበቅ፤

4/ To exchange or transfer Peer and equivalent work positions to other higher education institutions in the same professional field and position with the agreement of the institutions;

5/ To have academic freedom while supporting and working in research and teaching;

6/ Getting overtime payment for extra work hours;

7/ To participate in the planning and evaluation of the institution's mission in together with education departments, colleges, faculties, teaching hospitals and research centers.

## 6. Obligations of Academic Technical Assistant

Academic Technical Assistant has the following Obligations:

1/ Identifying the educational content for practical education and facilitating the resources and organization to ensure that the education is given properly;

2/ To carry out the tasks expected in the workshops, laboratories, teaching hospitals, centers of excellence, industries where students learn practical education, research and community service in the fields of public government higher education institutions;

3/ Prepare different types of manuals for practical education and make them available for use; and reviewing and making corrections to prepared manuals;

4/ Make the laboratory and field education advanced, efficient and effective by using technological development and improvement;

5/ Takeover, repair and maintain various laboratories and field workshop equipment's, to protect them from damage and waste;

፮/ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሥራቸው በሰውና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንዳያስከትል በኃላፊነትና በተጠያቂነት ማከናወን፤

፯/ የቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን በቤተ ሙከራና በመስክ የሚወስዱትን የተግባርና የመስክ ትምህርቶች ዓለማቀፋዊ ደረጃዎች በጠበቀ መልኩ እንዲማሩና እንዲመራመሩ የማገዝ፤

፰/ ጥናትና ምርምር ለሚሰሩም ሆነ መረጃ ለሚፈልጉ የተቋሙ የምርምር አካላት የላብራቶሪና የመስክ ውጤቶችን የመለካትና የመተንተን፤

፱/ ለተግባር ትምህርት የተገዙ ግብዓቶች ተገልጋዮች በጥንቃቄ እንዲጠቀሙ የማድረግ፤

፲/ በተቋሙ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ሥርዓት መሠረት የተግባር ትምህርት፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶችን የመደገፍ ፤

፲፩/ፕሮጀክት ለመስራት እንደ መነሻ ሀሳብነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ናሙና ፕሮጀክቶችን ለተማሪዎች መስራት፤

፲፪/ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ያላቸውን የተግባር እውቀት ክፍተት ለመሙላት ሳይንሳዊ እና ተግባራዊ ድጋፍ የማድረግ፤

፲፫/ የተማሪዎችን የተግባር ትምህርት ምዘና ውጤት ምስጢራዊነቱን የመጠበቅ ፤

፲፬/ በራሱ የሥራ አካባቢዎች ላይ የተጀምሩ ወይም ያላለቁ ሥራዎችና የተለያዩ አይነት ጥናቶችን ተገቢ ባልሆኑ ሰዎች እጅ እንዳይወድቁ በኃላፊነት የመጠበቅ፤

፲፭ ለተግባር ትምህርት የተገዙ ቁሳቁሶችን ተማሪዎች በጥንቃቄ እንዲጠቀሙ የማድረግ፣ ማስተካካልና ትክክለኛ ያልሆኑትን በማሻሻልና በማጠናከር በጥንቃቄ የመያዝ፤

6/ Give due care to human and environment and act responsibly and accountably while undertaking their tasks.

7/ Help undergraduate and postgraduate students to learn and doing research the practical and field lessons they take in the laboratory and field in accordance with International standards;

8/ Measuring and analyzing laboratory and field results for the research bodies in the institution, in order to doing research or seeking information;

9/ Ensuring that the learners use purchased resources for practical learning carefully;

10/ Support practical education, research and community services in accordance with the institution's mission, values and system;

11/ Create a variety of sample projects that serve as starting point for students;

12/ Providing scientific and practical support to students and researchers to fill the practical knowledge gap;

13/ Safeguarding the confidentiality of students' practical education assessment results;

14/ Be a responsible for protecting the started or unfinished works and different types of studies so that they do not fall into the hands of inappropriate people;

15/ Ensuring that students use materials purchased for practical learning carefully; correcting the incorrect ones by improving and strengthening them carefully, and as necessary;

፲፮/ በጥናትና ምርምር ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችና መረጃዎችን ስህተትና ችግር ያለባቸውን ለይቶ ውጤቱንም ለጥናትና ምርምር ማዕከል ሪፖርት ማድረግ ፤

፲፯/ ልዩ ፍላጎት የሚሹ ተማሪዎችን የመደገፍ እና የማብቃት፤

፲፰/ በተግባር ትምህርት መስጫ ቦታዎች ውስጥ የሚያስፈልግ ሥነ ምግባርና የጥንቃቄ አለባበስ ዘዴ ተግባራዊ የማድረግ ፤

፲፱/ ለቤተሙከራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥንቃቄና በተገቢ ጊዜ ከመጠቀሚያ ጊዜያቸው አኳያ በመለየት ለሚመለከተው ማዘጋጀትና ማቅረብ ፤

፳/ በሥራው ቦታ ያሉ ዕቃዎች በተገቢ ሁኔታ እንዲደራጁ ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### ፯. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት ትምህርት ተቋማት ኃላፊነትና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶች ኃላፊነት ተግባርና የሥራ ጫና እንዲሁም ዝርዝር መብትና ግዴታን የሚደነግግ መመሪያ ያወጣል ፤

፪/ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶችን የደረጃ እድገት መሰላል እና ጥቅማ ጥቅምን በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስወሰን በሥራ እንዲውል ያደርጋል አፈጻፀሙን ይከታተላል ፤

፫/ ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚስፈልጉ መመሪዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

16/ Identifying the errors and problems of the results and data obtained in the field of research studies and report the results to the research center;

17/ Supporting and capacitate students with special needs;

18/ Implement the method of etiquette and careful dressing required in practical education areas;

19/ Carefully prepare the materials needed for the laboratory according to their usage period and at the appropriate time and present to the concerned organ;

20/ Organize the materials in the workplace in a proper manner.

## Part Three

## Stakeholders' Duties and Responsibility

### 7. Duties and Responsibilities of the Ministry

The Ministry has the following Duties and Responsibilities

1/ Issuing Directives that stipulate the responsibilities, tasks and workload as well as detailed rights and obligations of academic technical assistants;

2/ Studying the promotion and benefits of academic technical assistants, presenting to the concerned body in order to make a decisions and monitor its performance.

3/ The Ministry may, issues Directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

**፰.<u>የከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት ኃላፊነትና ተግባር</u>**

ከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት ኃላፊነትና ይኖራቸዋል፡-

፩/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ ቅጥር መፈጸም፣የደረጃ ዕድገት መስጠት ፣ማዛወርና ማሰናበት፤

፪/ የተቋሙን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳቶች የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

፫/ የውስጥ የዲስፕሊን ደንብ በማውጣት እና የቅሬታ አፈታት ሥርዓትን አሳታፊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

**፱.<u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**8. <u>Duties and Responsibilities of Higher Governmental Education Institutions</u>**

The Higher Governmental Education Institutions has the following Duties and Responsibilities:-

1/ Employing, promoting, transferring and dismissing based on the needs ,according to the detailed Directives issued by the Ministry;

2/ Providing short and long term training for academic technical assistants based on the needs of the institution;

3/ Establishing internal disciplinary rules and implementing a grievance redressed system in a participatory manner.

**9. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any Regulations, Directives or practices inconsistent with this Regulation shall have no effect on matters cover under this Regulation.

**10. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter in to force on the date of publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 3rd Day of May 2023.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**